# የረመዷን ወር 1



ነቢዩ صَلَّى ٱللَّٰهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

# “መጣላቹሁ ረመዷን የተባረከው ወር።”

ነሳኢ ሶሂህ ብለውታል (2105)

አተ−ውሒድ.ኮም

# የረመዳን ወር 2



ነቢዩ صَلَّى ٱللَّٰهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

“ከናንተ ውስጥ ማንም ቢሆን **ከረመዳን** አስቀድሞ **አንድም ቀን** ቢሆን ወይንም **ሁለት ቀን እንዳይፆም።** **ነገር ግን** ያስለመደው ፆም ካለ መፆም ይችላል።”

ቡኻሪ(1914) ሙስሊም(1082) ዘግበውታል

# የረመዳን ወር 3



አማር ኢብኑ ያሲር رضي الله عنه እንዲህ ብለዋል፡

## “በአጠራጣሪ ቀናቶች ውስጥ የፆመ በቃሲም አባት ﷺ ላይ አስተባብሏዋል።”

ነሳኢ ሶሂህ ብለውታል (2187)

አተውሒድ.ኮም

# የረመዳን ወር 4



ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

"ኢስላም የተገነባው

በአምስት ነገሮች ላይ ነው እነሱም፡-

ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩን እና ሙሀመድ መልዕክተኛ መሆናቸውን በመመስከር፣ ሰላትን አዘውትሮ መስገድ፣ ዘካን መስጠት ሀጅ ማድረግ፣

**ረመዳንን መፆም ናቸው።"**

ቡኻሪ (8) ሙስሊም (16) ዘግበውታል

አተ-ውሒድ.ኮም

# የረመዳን ወር 5



ነቢዩ صَلَّى ٱللَّٰهُ عَلَيۡهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

**“አምስቱ ሰላቶች፣ ከጁምዓ እስከ ጁምዓ፣ ከረመዳን እስከ ረመዳን በመካከላቸው ያሉትን ኃጢአቶች ያብሳሉ ታላላቅ ወንጀሎችን ሲቀር።”**

ሙስሊም ዘግበውታል (233)

አተ-ውሒድ.ኮም



ነቢዩ صَلَّى ٱللَّٰهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

“ጨረቃን ካልታያችሁ ፃምን አትያዙ። ጨረቃንም ካልተመለከታችሁ ፃምን አትፍቱ። በናንተ ላይ ከተሰወረባችሁ ወርቹን ሰላሳ ሙሉ።”

ቡኻሪ(1906) ሙስሊም(1080) ዘግበውታል



# የረመዳን ወር 7

ነቢዩ صَلَّى ٱللَّٰهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

"የረመዳን ወር ሲገባ
የሰማይ በሮች ይከፈታሉ
የጀሃነም በሮች ይዘጋሉ
ሸይጣኖችም ይታሰራሉ"

ሙስሊም ዘግበውታል (1079)

አተ−ውሒድ.ኮም



# የረመዳን ወር 8

ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦

“የመጀመሪያው የረመዳን ሌሊት በሆነ ግዜ ጂኒና ሸይጣናት ይታሰራሉ። የጀሀነም በሮች ሳይከፈቱ ይዘጋሉ። የጀነት በሮች ሳይዘጉ ይከፈታሉ። ተጣሪው ይጣራል፦ መልካም ፈላጊ ሆይ ና፤ ተሰብሰብ ጠጋ በል። ሸር ፈላጊ ሆይ ተመለስ (ሸርህን አቁም) ይላል። ረመዳን እስኪያልቅ ድረስ በየቀኑ አላህ ከእሳት ነፃ የሚያወጣቸው ባሮች አሉት።”

ቲርሚዚ ዘግበውታል (682)

አተ−ውሒድ.ኮም

# የረመዳን ወር 9



ነቢዩ صَلَّىٰ ٱللَّٰهُ عَلَيۡهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፦

**“ስሁርን ተመገቡ ሱሁርን መመገብ በረከት አለበትና።”**

ቡኻሪ(1923) ሙስሊም(1095) ዘግበውታል

# የረመዳን ወር 10



ነቢዩ صَلَّى ٱللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

## “አላህና መልአክቶች ሱሁሩን በሚመገቡ ላይ ዱአ ያደርጋሉ።”

ሶሂህ አተርጊብ (1066)

# የረመዳን ወር 11



ነቢዩ صَلَّىٱللَّهُعَلَيْهِوَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

## “የሙእሚን መልካሙ ሱሁር ቴምር ነው።”

ሶሂህ አተርጊብ (1072)

አተ-ውሒድ.ኮም



# የረመዳን ወር 12

ነቢዩ صَلَّى ٱللَّٰهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

## “በእኛ ፆምና በአህለል ኪታቦች ፆም መካከል ያለው ልዩነት ሱሑር መብላት ነው።”

ሙስሊም ዘግበውታል (1096)

አተ−ውሒድ.ኮም

## የረመዳን ወር 13



ነቢዩ صَلَّىٰ ٱللَّٰهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

# “አንዳችሁ አዛን ሲሰማ በእጁ ላይ አንዳች ነገር ካለ የያዘውን ሳይጨርሰው እንዳይመልሰው።”

አቢ ዳውድ ሶሂህ ብለውታል (2350)

አተ−ውሒድ.ኮም



# የረመዳን ወር 14

ዘይድ ኢብኑ ሳቢት رَضِيَ ٱللَّٰهُ عَنْهُ ሲናገሩ፦

“ከነቢያችን صَلَّى ٱللَّٰهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ ጋር **ሱሁር** ከተመገብን በኋላ ሱብሂ ሰገድን ብለው ሲናገሩ በመካከላቸው የነበረው ወቅት ምን ያህል ነበር? ብለው ጠየቋቸው። እሳቸውም ሀምሳ የቁርአን አንቀፆች የሚያስነብብ ወቅት ነበር” አሉ።”

ቡኻሪ(1921) ሙስሊም(1097) ዘግበውታል



# የረመዳን ወር 15

## ከጎህ በፊት ለፆም መነየት ግዴታ ነው

ነቢዩ صَلَّى ٱللَّٰهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

**"ከጎሕ በፊት ፆምን ያልወሰነ ፆሙ ትክክል አይደለም።"**

አቢ ዳውድ ሶሂህ ብለውታል (2454)

አት-ተውሒድ.ኮም



# የረመዳን ወር 16

## አኢሻ እና ኡሙ ሰለማ رَضِيَ ٱللَّهُ عَنْهُمَا እንደሚናገሩት፦

"ነቢዩ صَلَّىٰ ٱللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ጁኑብ ሆነው ፈጅር ይደርስባቸው ነበር። ከዛ ይታጠቡና ፆም ይቀጥሉ ነበር።"

ቡኻሪ ዘግበውታል (1925)



# የረመዳን ወር 17

ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-

**“በአላህ መንገድ ላይ ሆኖ የፆመ ያቺን የፆመበትን ቀን የሰባ አመት (ጉዞ) ርቀት ያህል ፊቱን ከእሳት ያርቅለታል”**

ቡኻሪ(2840) ሙስሊም(1153) ዘግበውታል

# የረመዳን ወር 18



ነቢዩ صَلَّىٰ ٱللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

“የረመዳንን ፃም ግዴታ መሆኑን አውቆ (በኢማን) ምንዳም አገኘበታለሁ ብሎ (በኢሕቲሳብ) የፃመ ሰው ያለፈው ወንጀሉ ሁሉ ይማርለታል።”

ቡኻሪ(2014) ሙስሊም(760) ዘግበውታል



# የረመዳን ወር 19

ነቢዩ صَلَّى ٱللَّٰهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

## “ፆም ጋሻ ነው። ከእሳት መጠበቂያ ምሽግ ነው።”

ሶሂህ አልጃሚዕ (3880)

# የረመዳን ወር 20



ነቢዩ صَلَّىٰ اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

“አላህ እንዲህ ይላል፡- የአደም ልጆች ሥራቸው ሁሉ ለራሳቸው ነው። **ፆም ብቻ ሲቀር** ፆም የኔ ነው **ምንዳውንም የምከፍለው እኔው ነኝ አለ።**”

ቡኻሪ(1904) ሙስሊም(1151) ዘግበውታል



ነቢዩ صَلَّىٰ ٱللَّٰهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

“ፆም እና ቁርአን የቂያም ቀን ለአላህ ባርያ ዋስ ይሆናሉ። ይኸውም ፆም ይላል፡- ጌታዬ እኔ በቀን ከምግብና ከስሜቱ ከለከልኩት ዋስ ሆኛለሁና ዋስትናዬን ተቀበለኝ ይላል፣ አሉ።”

ሶሂህ አልጃሚዕ (3882)



# የረመዳን ወር 22

ነቢዩ صَلَّىٰ ٱللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

## “እጁ አመድ አፋሽ ይሁን ረመዳንን አገኝቶ ወንጀሉ ሳይማርለት ያለፈው።”

ቲርሚዚ ሶሂህ ብለውታል (3445)



# የረመዳን ወር 23

ነቢዩ صَلَّىٱللَّهُعَلَيۡهِوَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

“ጀነት ውስጥ ረያን የሚባል ፃመኛ የሚገባበት በር አለ። በዚህም በር የቂያም ቀን ፃመኞች ከገቡበት በኋላ በሩ ይዘጋል። ካለነሱም በስተቀር ማንም አይገባበትም።”

ቡኻሪ(1896) ሙስሊም(1152) ዘግበውታል

# የረመዳን ወር 24



ነቢዩ صَلَّىٱللَّهُعَلَيۡهِوَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፦

# “የፃመኛ ሰው የአፉ ጠረን ከአላህ ዘንድ ከምስክ (ሽቶ) ሽታ የተሻለ ይሆናል።”

ነሳኢ ሶሂህ ብለውታል (2214)

አተ-ውሒድ.ኮም



# የረመዳን ወር 25

ነቢዩ صَلَّىٱللَّهُعَلَيۡهِوَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

**“አላህ በረመዳን በሁሉም ቀንና ሌሊቶች ከእሳት ነፃ የሚላቸው አሉ። ለሁሉም ባሪያ ደግሞ ለሱ ተቀባይነት ያለው ዱዓ አለው።”**

ሶሂህ አልጃሚዕ (2169)

አተ-ውሒድ.ኮም



# የረመዳን ወር 26

ነቢዩ صَلَّىٰ ٱللَّٰهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

“አላህ በሁሉም የረመዳን (የኢፍጣር ቀን) እንዲሁም ሌሊት ከእሳት ነፃ የሚላቸው አሉ።”

ሶሂህ አልጃሚዕ (2166)

አተ−ውሒድ.ኮም





ነቢዩ صَلَّىٱللَّٰهُعَلَيۡهِوَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

**“ፆም ማለት ከምግብና ከመጠጥ መቆጠብ ብቻ አይደለም። ፆም ማለት ከአስነዋሪና ከአስቀያሚ ነገር መቆጠብ ነው።”**

ሶሂህ አልመዋሪድ (741)



# የረመዳን ወር 28

ነቢዩ صَلَّىٱللَّهُعَلَيۡهِوَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

“የሐሰት ንግግርን በሐሰት መስራትን እንዲሁም መሀይምነትን (የመሐይማንን ተግባር) ያልተወ ሰው ምግቡንና መጠጡን ከመተዉ አላህ ጉዳይ የለውም።”

ቡኻሪ ሶሂህ ብለውታል (1903)



ነቢዩ صَلَّىٰ اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

“አንዳቹህ በሚፃምበት ቀን
እንዳይረክስ እንዳይጮህ
እንዳይሞኝም አንዱ
ቢሰድበው ወይንም ቢጣላው
እኔ ፆመኛ ነኝ ይበል።”

ቡኻሪ(1904) ሙስሊም(1151) ዘግበውታል



## የረመዳን ወር 30

ነቢዩ صَلَّى ٱللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

# “(ውዱእ ስታደርግ) ፆመኛ ካልሆንክ በአፍንጫህ በደምብ ሳብ”

አቢዳውድ ሶሂህ ብለውታል (2366)



# የረመዳን ወር 31

ኢብኑ አባስ رضي الله عنه ሲናገሩ፦

“ነቢዩ ﷺ መልካምን በመቸር አቻ አልነበራቸዉም። በተለይ በረመዳን ከጅብሪል ጋር ሲገናኙ ቸርነታቸው እጅግ ይጨምራል። ጅብሪል በየረመዳኑ እየመጣ ቁርአንን ይማማሩ ነበር።”

ቡኻሪ(1902) ሙስሊም(2308) ዘግበውታል



# የረመዳን ወር 32

ነቢዩ صَلَّىٰ ٱللَّٰهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

“ፃመኛ መሆኑን ዘንግቶ የበላ ወይም የጠጣ ፃሙን ይሙላ። የመገበውና ያጠጣው አላህ ነው።”

ሙስሊም ሶሂህ ብለውታል (1155)

አተ-ውሒድ.ኮም



# የረመዳን ወር 33

ነቢዩ صَلَّىٰ ٱللَّٰهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፦

**“አንድን ፆመኛ ያስፈጠረ ሰው ካስፈጠረው ፆመኛ ምንም ሳይቀንስበት ያስፈጠረውን ፆመኛ ያህል አጅር (ምንዳ) ያገኛል።”**

ሶሂህ አልጃሚዕ (6415)

አተ−ውሒድ.ኮም

# የረመዳን ወር 34



ነቢዩ صَلَّى ٱللَّٰهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

“ለፆመኛ ሁለት ደስታዎች አሉት። ደስታዎችም፦ ፆመኛ ማታ ሲያፈጥርና በአኼራ ጌታውን ሲገናኝ ነው።”

ሙስሊም ሶሂህ ብለውታል (1151)

የረመዳን ወር 35



አነስ رَضِيَ ٱللَّٰهُ عَنْهُ እንደሚናገረው፡-

# “ነቢዩ صلى الله عليه وسلم

# በቴምር በማፍጠር

# የሚጀምሩ ነበሩ።”

ሲልሲለቱ አሶሂሃ (2117)



# የረመዳን ወር 36

ነቢዩ صَلَّى ٱللَّٰهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

# “ሰዎች ፍጡር ላይ እስከቸኮሉ ድረስ ከመልካም አይወገዱም።”

ቡኻሪ(1957) ሙስሊም(1098) ዘግበውታል



# የረመዳን ወር 37

አብደላህ ኢብኑ ዑመር رضي الله عنه እንደሚናገረው፦

ነቢዩ ﷺ ባፈጠሩ ግዜ ይህን ዱዓ ይሉ ነበር፦ “ዘሃበ ዘመኡ ወብተለተል ዑሩቅ ወሰበተል አጅር ኢንሻ አላህ”

ትርጉም፦ “ጥም ተወገደ የደም ሥር ተብሏል የአላህ ፍላጎት ከሆነ ምንዳውም ፀደቀ ማለት ነው።”

ሶሂህ አልጃሚዕ (4678)

አተ-ውሒድ.ኮም

# የረመዳን ወር 38



ነቢዩ صَلَّىٰ ٱللَّهُ عَلَيۡهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

**“የረመዷንን ወር በኢማንና ከአላህ ብቻ አጅርን በመፈለግ የቆመ ሰው ከዚህ በፊት የሰራው ወንጀል በሙሉ ይማርለታል”**

ቡኻሪ(2009) ሙስሊም(759) ዘግበውታል

አተ−ውሒድ.ኮም



# የረመዳን ወር 39

ነቢዩ صَلَّى ٱللَّٰهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

“የለይለተል ቀድርን በኢማንና ከአላህ አጅር በመፈለግ የቆመ ከዚህ በፊት የሰራው ወንጀል በሙሉ ይማርለታል።”

ቡኻሪ(1901) ሙስሊም(760) ዘግበውታል



ነቢዩ صَلَّى ٱللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

# “ለይለቱል ቀድርን በመጨረሻ አስር የረመዳን ቀናቶች ውስጥ ፈልጉት።”

ቲርሚዚ ሶሂህ ብለውታል (792)



አዒሻ رَضِيَ ٱللَّهُ عَنْهَا እንዲህ ትላለች፡-

“ነቢዩ ﷺ በረመዷን ወር **የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት** በመስጊድ ውስጥ ይቀመጡ ነበር (ኢእቲካፍ) ያደርጉ ነበር።”

ቡኻሪ ሶሂህ ብለውታል (2033)

# የረመዳን ወር 42



አዒሻ رَضِيَ ٱللَّهُ عَنْهَا እንዲህ ትላለች፡-

“ነቢዩ ﷺ ከረመዳን የመጨረሻዎቹ አስርት ቀናት ከሌላ ጊዜ በተለየ መልኩ (በዒባዳ) ላይ ይተጉ ነበር።”

ሙስሊም ሶሂህ ብለውታል (1175)

አት-ተውሒድ.ኮም



አዒሻ رَضِيَ ٱللَّهُ عَنْهَا እንዲህ ትላለች፡-

“ነቢዩ ﷺ የመጨረሻዎቹ የረመዷን ወር አስር ቀናት ሲገቡ ሌሊቱን በሙሉ በሰላትና በፀሎት ያሣልፉ ነበር ቤተሰቦቻቸውንም ለኢባዳ ይቀሰቅሱና ወገባቸውን ታጥቀው ለኢባዳ ይነሣሱ ነበር።”

ሙስሊም ሶሂህ ብለውታል (1079)



አኢሻ رَضِيَ ٱللَّهُ عَنۡهَا እንደምትናገረው የአላህ መልእክተኛን ﷺ ለይለተል ቀድር እንደሆነ ከተሰማኝ ምን እንደምል አሳውቁኝ ስላቸው እንዲህ በይ አሉኝ:-

“አላህ ሆይ አንተ በርግጥም ይቅር ባይ ነህ ይቅር ማለትን ትወዳለህ ስለሆነም ለኔ ይቅር በለኝ።”

ኢብኑ ማጃህ ሶሂህ ብለውታል (3119)



# የረመዳን ወር 45

ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦

“በረመዳን ዑምራን መፈፀም ከሐጅ ጋር ይስተካከላል። ወይም ደግሞ ከእኔ ጋር ሐጅ እንደማድረግ ነው።”

ቡኻሪ(1863) ሙስሊም(1256) ዘግበውታል



አብደላህ ኢብኑ ዑመር رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُ
እንዲህ ብለዋል፦

“የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ዘካተል ፊጥርን ከተምር ወይም ከገብስ አንድ <ሷዕ> በእያንዳንዱ ሙስሊም፤ ባሪያ፣ ጨዋ (ባሪያ ያልሆነ)፣ሴት፣ ህፃን፣ አዋቂ ላይ ግዴታ አድርገዋል። እንዲሁም ሰዎች ወደ (ዒድ) ሰላት ከመውጣታቸው በፊት ለሚገባቸው ሰዎች እንዲደርስ አዘዋል።”

ቡኻሪ ሶሂህ ብለውታል (1503)



ነቢዩ صَلَّى ٱللَّٰهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፦

# “ረመዳንን ፆሞ የሸዋልን ስድስት ቀናት ፆምን ያስከተለ አመቱን ሙሉ እንደፆመ ይቆጠራል።”

ሙስሊም ሶሂህ ብለውታል (1164)



# የረመዳን ወር 48

ነቢዩ صَلَّىٰ ٱللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ እንዲህ ብለዋል፡-

“ከረመዳን እስከ ረመዳን ባለው በየወሩ ሶስት ቀናት የሚፆም አመት ሙሉ እንደፆመ ይቆጠራል።”

ሙስሊም ሶሂህ ብለውታል (1162)

# ረመዳንን አስመልክቶ የሚነገሩ ትክክለኛ ያልሆኑ ሀዲሶች

1- ((ረመዳን የመጀመሪያው የእዝነት የመሀከለኛው የምህረት የመጨረሻው ከእሳት ነፃ የመውጫ ነው።))
ሙንከር (ሲልሲለቱ አዶዒይፍ: 1569)

2- ((ፁሙ ጤናማ ትሆናላችሁ።)) ዶዒፍ (ሲልሲለቱ አዶዒይፍ: 253)

3- ((ባሮች የረመዳንን ዋጋ ቢያውቁ ኖሮ ኡመቶቼ አመቱን ሙሉ ረመዳን እንዲሆን ይመኙ ነበር።))
መውዱእ (ዱዒይፍ አተርጊብ: 596)

4- ((አላህ ሆይ ረጀብንና ሻዕባንን ባርክልን ረመዳንን አድርሰን።))
ዶዒፍ (ዶዒፍ አልጃሚዕ: 4395)

5- ነቢዩ ﷺ ባፈጠሩ ግዜ ይህን ዱዓ ይሉ ነበር:- ((አላሁመ ለከ ሰምቱ, ወአላ ሪዝቂከ አፍጠርቱ። አላህ ሆይ! ለአንተ ፆምኩ:: በአንተ ሲሳይም (ሪዝቅ) አፈጠርኩኝ።))
ዶኢፍ (ዶዒፍ አልጃሚዕ: 4349)

6- ((የፆመኛ በቀን መተኛት ኢባዳ ነው።)) ዶዒፍ (ሲልሲለቱ አዶዒይፍ: 4696)

7- ((ረመዳን አትበሉ ረመዳን ከአላህ ስሞች አንዱ ስም ነው። ነገር ግን የረመዳን ወር በሉ።))
ባጢል (ሲልሲለቱ አዶዒይፍ: 6768)